# ግብፅ በአባይ ላይ የምታሳየው ትዕቢትና እብሪት የውሃ ጥቅሞቿን አያስከብሩላትም

**ብርሃኑ አበጋዝ***

(ግንቦት 9/2012)

በድንበር አላፊ ተፋሰሶች የመጠቀም ሉዓላዊ መብትን በተመለከተ የግብፆች ተረትና የሥነ-ልቡናዊ ዕምነት ከሁሉም ማስረጃዎች አንፃር በተቃርኖ የሚያዝ ከንቱ ስሜት ነው። በሥነ-ልቡና አገላለጽ እውን ያልሆነ፣ ማስገረሙ አንዳንዴም ማሳቁ ያልቀረ፤ ለላይኛው የናይል ተፋሰስ አገር ህዝቦች ዕድለ ቢስነት በጭራሽ የማያቋርጥ ደንታ አልባ የሆነ፣ በሌሎች ሃብት የብቻ ተጠቃሚነት አመለካከትን ያቀፈ ፤ እንዲሁም የቅኝ-ግዛታዊ ስሜት የለከፈው አዕምሯዊ የመዛባት ስብዕናን የሚያጋልጥ ነው።

ይህ ጉዳይ ደግሞ ነፃነት ወዳጆች በሆኑት ኢትዮጵያውያን ምልከታ በጎስቋላው ድህነታቸው አቅም ለሺህዎች ዓመታት ለዛሬዎቹ ሱዳንና ግብፅ ዕድገትና ልማት ያደረጉት የውድ ግዴታ ድጎማ በገንዘብ ቢተመን አስደንጋጭ ነው። ይታያችሁ:- ከጥንት ግሪኮች ጀምሮ ግብፅ የአባይ ስጦታ ትባላለች። ሆኖም አባይ ደግሞ የኢትዮጵያ ስጦታ ነው። አማራጭ የለሽ ድምዳሜው <u>ግብፅ የኢትዮጵያ ስጦታ ናት ማለት ነው</u>! 80 በመቶ የሚሆነውን ውሃዋንና በምንም የማይተመነውን ውድ አፈር በየአመቱ የምትቀበለውና ምስጋና ቢሷ ግብፅ ኢትዮጵያን እንደ እናት ማየት ተስኗት ይባስ ብላ ስታቆረቁዛት ቆይታለች። ቀጥላለችም።

የፕሮፌሰር መሃመድ ናስር ኤል ዲን አላም የቅርብ ጊዜ ሐተታ (አህራምኦንላይን፣ ሜይ 10፣12 እና 13፣ 2020) ትዕቢትና ንቀት የተቀላቀለበት ኦፊሴላዊ መሳይ ፕሮፓጋንዳ ታስቦበትና ሆን ተብሎ የተደረገ፣ የኢትዮጵያን አሳማኝ ማብራሪያ በተዛባና በአሳሳች ገጽታ ለማቅረብ የተዘጋጀና ጉዳዩን ጠንቅቀው ከሚያውቁት ሁሉ የማይጠበቅ መልዕክት ነው። በቅንነት በሚያስቡ አንባቢዎች ዘንድ የግብፅ መንግስታት የብቸኛ ተጠቃሚነትን በዘላቂነት በማስቀጠል ቅዠት መዋዠቃቸው የአደባባይ ምስጢር ከሆነ ውሎ አድሯል። ከሞኝ ቤት ሞፈር ይቆረጣል እንደሚባለው ይህን ሳያስተውሉ፣ የቀድሞው የውሀ ሀብትና መስኖ ሚኒስትርና መሰሎቻቸው የሚሰጧቸውን ስንኩል አስተያየቶች ያየ ተላላፊ አንባቢ ሸፍጡን አዙሮ ባያስተውል ይቅርታ ይደረግለታል። እውነታው ግን እንደሚከተለው ነው:-

- በዓለም ውስጥ ካሉት አብይ የውሀ ክልሎች ህጋዊ ዕውቅናና አጠቃላይ የውሃ ስምምነት የሌለው የአስራ አንድ ተፋሰስ አገሮች ንዋይ የሆነው ናይል ብቻ ነው። ሱዳንንና ግብፅን በተናጠል ያሳተፈው የ(1929) የቅኝ ግዛት ዘመን ስምምነትና የ(1959) ተጓዳኝ ሁለትዮሽ ስምምነት በኢትዮጵያ እውቅና ስላልተሰጣቸው ዛሬ ፉርሽ ናቸው። ይባስ ብለው እነዚህ ሁለት በሰው ሃብት አልቃሽ አገሮች በናይል ተፋሰስ ተጋሪ አገሮች ድርድር (Nile Basin Initiative) በዋናዎቹ ሰነዶች ላይ ፈርመው ሲያበቁ እማክተሚያው ውል ላይ ሊደረስ ሲል በመጨረሻዎቹ ሰዓታት ማሽግሽጋቸው በተለይ የግብፅን የአፈንጋጭነት እኩይ ቋሚ ስልት የሚያጋልጥባት ነው።
- የታላቁን ህዳሴ ግድብ በመሙላት ዕቅድ ላይ ግብፅና ሱዳን ግብዓታቸውን እንዲያያቀርቡ ተጋበዙ፣ እነርሱ ግን የየራሳቸውን ግድቦች ሲገነቡ ወይም ውሃውን ወዳልተገባ አቅጣጫ ሲወስዱ (ለምሳሌ የቶሽካ ቦይና ክምችት) ኢትዮጵያን ሳያማክሯት ነበር። ይህም የኢትዮጵያን ቅንነት ቢያሳይም ብልጣብልጦቹ ግን እንደሞኝነት ወስደውታል።
- የመሀመድ አሊዋ ግብፅ፣ የአባይን መነሻ በቁጥጥር ይዛ ለመኖር ቁምጣ ሁለት ጊዜ የቀጥታ ጦርነት ወረራ አድርጋ ተሸንፋለች። ኢትዮጵያ በውሃ ሀብቷ ሳትጠቀም በክና እንድትቀር፣ የፖለቲካ መረጋጋት አጥታ በቁሟ እንድትሞት ግብፅ የምታደርገው ገደብ-የለሽ ጥረት፣ እንዲሁም ኢትዮጵያ ውሃዎቿን ለማልማት የፋይናንስ ድጋፍ እንኳ እንዳታገኝ እያደረገችው ያለው የዘመናችን ዲፕሎማሲያዊ ዘመቻ የቅርብ ጊዜ ምሳሌዎች ናቸው። ግብፅ በማያስገርምና በማይማርክ ሁኔታ ከሚያስፈልገው በላይ የምታሳየው ዲፕሎማሲያዊ ሽር-ጉድና በወታደራዊ ኃይል ማስፈራራት ለኢትዮጵያዊያን ያን ያህል ግድ አልሰጠንም፤ የግብፅን ወታደራዊ ብቃትና የጂኦፖሊቲካል ተፅዕኖ ክህሎቶችን ብንገነዘብም።

ግብፃውያን ለህልውናቸው በናይል ውሀ ላይ ያላቸውን ከፍተኛ ጥገኝነት ኢትዮጵያውያን እንደምናከብርላቸው እሙኑኝ። ደግን ልጅ እናቱም አትወደውም እንዲሉ በግብርም አሳይተነዋል። ነገር ግን እኛ ኢትዮጵያውያንም ድህነትን የታሪክ አተላ ለማድረግ ቆርጠን መነሳታችንን ወዳጅም ጠላትም እንዲረዳው ያስፈልጋል። የግብፅ ባለሥልጣናትና ምሁራን የኢትዮጵያን የሉዓላዊነት መብትና የድሆቿን ብዛት አውቀው ቸል ማለታቸው ፍጹም ግራ የሚያጋባ ነው፤ ሊወገዝ የሚገባውም ስንኩልነት ነው።

አባይ፣ ተከዜና ባሮ የናይል ገባሮች የጥቅመት ጉዳይ ሲነሳ፣ ግብፃውያን እየበሉና በብርሃናማ አካባቢ ሲኖሩ ኢትዮጵያውያን በረሃብ ቸነፈርና በጨለማ መኖራቸውን ይቀጥሉበት የሚለውን አስጠሊታ አስተሳሰብ ዛሬ የሚቀበል ማነው? ግብፅ በረሃ ስለሆነች የናየልን ውሀ መቶ በመቶ ይገባኛል ስትል፣ ኢትዮጵያም የሌላትን ግን መቶ በመቶ የሚያስፈልጋትን ዘይት ግብፅ ለመስጠት ለምን ፈቃደኛ አልሆነችም? ፍላጎት ብቻውን ወሳኝ ከሆነ ለምን ኢትዮጵያ ከአባይ ሌላ ባሉት ወንዞቿ ትጠቀም የሚለውን የብልጣብልጦች ክርክር እያቀረቡ በሌላ በኩል ደግሞ ፍልስጤማውያን ብዙ መሬታ ባላቸው በሌሎች የአረብ አገሮች እንዲኖሩ ይደረግ የሚል ኢፍታዊ ሃሳብ ሲራመድ አንድም ግብፃዊ የማይቀበለው? ወርቃማው ህግ የሚያስተምረውን ጥሰው በራሳቸው ላይ እንዲፈጸምባቸው የማይሹቱን ደካማን አስገድዶ በላተኛነትን ለምን በኢትዮጵያ ላይ ከመፈጸም አልፈው ዘላለማዊ ሊያደርጉት ይመኛሉ?

ሳይንሳዊ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከአዋሽ በስተቀር 90 በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ፈሳሽ ውሃ ድንበር ተሻጋሪ ነው። በተለይም ለግብፅ፣ ለሱዳንና ለሶማሊያ የህልውና መሰረት ነው። ስለዚህ የውዝግቡ ዋና መንስዔ "የሁሉን አዎንታ የተጎናጸፈ ሁለገብ የናይል ውል" አለመኖሩ ነው። በሁለቱ የአፍሪካ ሃያል አገሮች የሚኖረው ከ200 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ በጠባቡ የአባይ በሰፊው ደግሞ የናይል እኩል ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ወቅቱ አሁን ነው። በአለም አቅፍ ፍትሃዊ የወንዞች አጠቃቀምና እንክብካቤ ህግጋት የታነጸ ውል መፈራረም ዋናው መፍትሄ ነው። ለዚህም ሚኮንግ፣ዩፍሬቲስ፣ ጋንጅስ፣ ዳንዩብ፣ ኮሎራዶና ፓናማ የሚባሉትን ትልልቅ ወንዞች የሚያስተዳድሩትን ውሎች በአብነት ማጤን ጠቃሚ ነው።

ከአስር አመታት በፊት ተጀምሮ በግብፅ አፈንጋጭነት ያልተጨረሰውን "የትብብር ስምምነት ማዕቀፍ" የሚባለውን የናይል ተፋሰስ አገሮች የድርድር ይዘት ማክተም ያስፈልጋል። አዲሱ ውል በኢትዮያ ሕዝብ አወንታን ለማግኘት ሶስት አምዶችን ወይንም የብሩጨማ እግሮችን መቸከል ይኖርበታል፡-

1) <u>የናይልን ውሀ በፍትሃዊነት አብሮ መጠቀም።</u> ይህ ጉዳይ ግብፅን አንቆ የሚያዛት ነው። ምክንያቱም ግብፅ ይህን ስምምነት ከተቀበለች አሁን የምትጠቀመውን የናይል ውሃ ግማሹን ያህል ልታጣ ትችላለች። ብሎም፡-ውሃው ለሚመነጭባቸው ተፋሰስ አገሮች ከድርሻዋ በላይ

ማግኘት ከፈለገች በልዩ ስምምነት መግዛት አለባት ማለት ነው። በድርቅ ወቅት የቀነሰ ውሃን በእኩላዊነት ቅናሽ እንደምታገኝ መቀበልም ሊኖርባት ነው። ውሀ ከመጠን በላይ የሚወስዱ የሰብል አይነቶችንም (ለምሳሌ ጥጥ) ከማልማት ትገደባለች። እንዚህን የመሳሰሉ አዲስ ክስተቶችን ለመታደግ በግዴለሽነት የውሃ አቅጣጫዎችን የመቀልበስና በከንቱ በበርሃ ማትነን የሚያመጡ ፕሮጀክቶቿን ትተዋለች። የሜዲተራኒያን ባህር ወደ ግብፅ የደለል ምድር የሚያደርገውን ሰርጎ ማስገባት ለመቋቋም ስትገደድ ቸልተኛነቷን ታቆማለች። በኢትዮጵያ ከፍተኛ ምድሮች ላይ የሚገኙ ብዙ ትናንሽ ጅረቶች የሚደርስባቸውን መድረቅ ለመቀነስ በተራራ ሰንሰለቶች ላይ ለሚደረው ስራ ወጪ ለራሷ ረጅም ጥቅም ስትል ድርሻዋን እንድታበረክት ትገደዳለች። የራሷን እጅግ ከፍተኛ መጠን ያለውን የከርሰ ምድር ውሀንም እንደማካካሻ ለመጠቀምም ትገደዳለች።

2) <u>በናይል ተፋሰስ ውስጥ በሚገኙትና ወደፊት በሚሰሩት ግድቦች ላይ በጋራ ምርመራና እንክብካቤ ማድረግ።</u> በናይል ተፋሰስ ኢኒሽየቲቭ ውስጥ ሁሉም በኢኮኖሚ ረገድ ጠቃሚ ግድቦች ከቴክኒክና ከፋይናንስ ረገዶች አዋጭ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ መመሪያና መዋቅር መፈጠር አለበት። ትርኪስ ግድብ ለታች ተፋሳሽ አገሮችም ሆነ ለኢትዮጵያ ኪሳራ ናቸውና።

3) <u>የናይል ተፋሰስን ስነ-ምህዳር በጋራ ማደስና መንከባከብ።</u> በዓለም ከባቢ የሙቀት ጭመራና በህዝብና ገቢ እድግቶች ተጽእኖ ምንጮች ከደረቁና ተራራው ሁሉ ከተራቆተ አገር አቋርጦ የሚሄድ ወንዝ አይኖርምና! መዋቅሩ ቅቡልነትን ለመጎናጸፍ ትልቁ ናይል የሚነካቸውን ትንንሾቹንም ሆነ ትልልቆቹን አገሮች ማካተት አለበት። እንዲህ ሲሆን ብቻ ነው የቀጠናው መረጋጋትና ታዳጊውን የውሃ ፍላጎት በበቂ አቅርቦት ለማጣጣም የሚቻለው። በግልጽነት መሪዎቻቸውና ልሂቃኖቻቸው አዙረው ቢያዩት ኖሮ ግብፅንና ሱዳንን የሚገጥማቸው ትልቁ አደጋ ኢትዮጵያ ተገቢ ድርሻዋን ማግኘቷ ሳይሆን የኢትዮጵያ ከፍተኛ ምድሮች የሚሸፍኗቸው ዕፅዋት በፍጥነት እየጠፉና የአባይ ገባር ወንዞችም እየደረቁ፣ የጣና ሀይቅም በእንቦጭ አረም እየተወረረ በመታፈን ላይ መሆኑ ነው።

---

ዩጋንዳዊው መሪ ዩዌሪ ሙሴቪኒ ደጋግመው ፕ/ ሙባረክን 'አገርህ ግብፅ በጂኦግራፊም ሆነ በኢኮኖሚ መሰፈርቶች አፍሪካዊ መሆኗን ረስተሃል' ብየ አስጠንቅቁው ነበር ይላሉ። ስለዚህም የግብፅ

መሪዎች ደካማ ብለው የናቋቸውን (ነገር ግን ጉልበትና ድፍረት እያገኙ የመጡን) የላይ ተፋሰስ አገሮች ከማስፈራራት ይልቅ የሚበጃቸው እንደ ኢትዮጵያና ዩጋንዳ ያሉትን ኩሩ አገሮች በእኩልነት በመቀበል ወደ አፍሪካዊ የምክክር መድረክ እንዲመለሱ እንመክራቸዋለን። በግብፅ ውከላ ከሚያመደሙዱላት ኃያላን አገሮች ወይም ወዳጅ የአረብ መንግሥታት ይልቅ 'ለአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ' በእጅጉ ይመረጣል። ሁሉ ከተሞከረ በኋላ ለግብፅና ሱዳን ፍትሃዊ ምክክር የውድ ግዴታቸው መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው።

ግብፅ በአንጻራዊ አይታ አቅመኛ አገር መሆኗ አይካድም። ሆኖም ፍጹማዊ ልዕለ-ኃያል አይደለችም። ስለሆነም የተፈራች ሳትሆን የተከበረች ጎረቤት አገር ለመሆን ከፈለገች በሰጥቶ-መቀበል መርህ መፍትሄ ለማግኘት መጣር ይጠበቅባታል። ያም ሆነ ይህ ጥርጣሬ ውስጥ የሞይገባ እውነታ ግን እንደፈራችው ታሪካዊው የውሃ ድርሻዋ ይቀንስባታል። ግብፅ እንዲህ ካለው በሌሎች ሉዓላዊ አገሮች ሀብት ላይ ራሷ ባቻ የመወሰንን የሱስ አባዜ አንጥራ ወርውራና ከአጣብቂኙ አምልጣ ሙሉ ኢንዱስትሪያዊነትና ዘመናዊ አገልግሎት ሰጪነት ወዳለው የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን ላይ ብትረባረብ ያዋጣታል። ኢትዮጵያም እንዲሁ። ይህ ከሆነ ብቻ ነው ግብፅ ታላቁን የናይል ሸለቆ በመምራት ለአካባቢው ሕዝብ ሰላምን፣ አርነትንና ብልጽግናን ለማውረድ ትልቅ ሚና ልትጫወት የምትችለው፤ የታላቅነት ክብርንም የምትጎናጸፈው።

=======================

(*) የዚች አስተያየትና ትንተና አቅራቢው በአሜሪካ ዊሊያምና ሜሪ ዩኒቨርስቲ የስነ-ሃብት (ኢኮኖሚክስ) ሙሉ ፕሮፌሰር ናቸው። ወደ አማርኛ ተርጓሚውን አቶ አያሌው ምትኩን ከልብ ያመሰግናሉ። በካፒታል ኢትዮጵያ፣ ዘሃበሻና፣ ቦርከና በሚባሉ ድረገጾች ላይ ቀደም ብሎ በእንግሊዝኛ ታትሟለች።